★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞ ቅጽ 42 ቁ. 5** **መጋቢት/ ሚያዚያ 2009 ዓ.ም**

# ተደራጅቶ መታገል በኢሕአፓ

ለህይወታቸው ሳይሳሱ የሞትን ፅዋ እየተጎነጩ ፤ አገራቸው የጣለችባቸውን አደራና ግዴታ ፈፅመው ያለፉት እኚያ የኢሕአፓ ጀግኖች ባለታሪኮች ናቸው። ለትውልድና ለታሪክ እንዲተላለፍ የትውልዱ የጀግንነት ታሪክ ሳይበረዝና ሳይሸራረፍ ተጠብቆ መቆየት ያለበት ከመሆኑም በላይ ለተተኪው ትውልድ የማስተላላፍ ታሪካዊ ሃላፊነት የወደቀው በቀዳሚው ትውልድ ትከሻ ላይ መሆኑን መረዳት የግድ ይላል።

እነዚያ ጀግኖች የፈፀሙትን ተጋድሎና የከፈሉትን መስዋዕትነት ስንዘክር ሁሌም ከፊታችን የሚደቀነው ማንም ሳያሳስባቸው፤ ማንም ደሞዝ ሳይከፈላቸው፤ ማንም ትእዛዝና ማዕርግ ሳይሰጣቸው በህይወታቸው የከፈሉት አገራዊ መስዋዕትነት መሆኑን ነው። ከእነሱ የምንማረው አገሩን አፍቃሪና ሕዝቡን አክባሪ የሆነ ዜጋ ትግልና ሩጫው ሊሆን የሚገባው ለትውልድና ለአገር የሚበጁ አገራዊ እሴቶችን ተንከባክቦና ጠብቆ የማይሞትና የማያልፍ ቁም ነገርን ለተተኪው ትውልድ አውርሶ ማለፍ ነው።

የትናንት ቆራጥ ጀግኖች ይህንን የማይናወጥ ቃል ኪዳን መመሪያቸው አድርገው ሀገራቸው የጠየቀቻቸውን ክቡር መስዋዕትነት በመክፈላቸው ነው ዛሬ፤ የዚያ ታሪክ፣ የዚያ ባህል፣ የዚያ ቅርስ ባለቤቶች ነን፤ ባለ ሀገር ነን፤ እያልን በልበ-ሙሉነት በማንነታችን ልንኮራ የቻልነው። ዛሬም ቢሆን ከትግል ውጭ የሀገርን ክብርና የሕዝብን መብት ማስጠበቅ አይቻልም። የሀገር ሉዓላዊነትና የሕዝብ ጥቅም ሊከበር የሚችለው ኃላፊነትንና አደራን ሊሸከም የሚችል አገር ወዳድ፤ ቆራጥና ታጋይ የሆነ ትውልድ ሲኖር ነው። የዚያን ዘመኑ አፍላ ትውልድ የለውጥን አስፈላጊነት አምኖበት የታገለው የሚወዳት ሀገሩ ጠንካራና የበለፀገች፤ ፍትህና ርትዕ የሰፈነባት፤ በረሃብና በበሽታ ዜጎችዋ የማይረግፉባት፤ እኩልነት የተከበረባት የሁሉም ዜጎች አገር እንድትሆን ከልቡ በመመኘት ነው።

ከእኩልነት ጥያቄ ጋር ተያይዘው ላሉት ችግሮች መፍትሔ ለመሻት የጣረው ሀገር ወዳዱ ትውልድ፤ ለራሳችን ችግር ራሳችን ምላሽ እንስጥ ብሎ ነበር የተነሳው። የሕዝብ አንድነት በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ እንዲመሰረት ቀሰቀሰ፤ የራሱን ብሔርሰብ ሳይከልል፤ በብሔረሰብ ደረጃ ሳይሆን ዜጎች በኢትዮጵያዊነት እየተደራጁ ባዕዳን ሰርገው የሚገቡበትን ቀዳዳ ለመድፈን ጣረ። እንደሰጎን አንገታቸውን ቀብረው፣ የብዙኅኑን ብሶት ረግጠው፣ በእኩልነት መኖርን አሻፈረኝ ብለው፤ በኃጥ መደራጀትን ፈልገው፤ በቅኝት ምናብ ውስጥ እንደዋዠቁት - ዛሬም እንደሚዋዥቁት - አልቃዡም። የሀገርና የሕዝብ አንድነት ሊጠበቅና ሊጠናከር የሚችለው በጥላቻ ሳይሆን በፍቅር፤ በጭቆና ሳይሆን በዴሞክራሲ፤ በእኩልነትና በሕዝብ መብት መረጋገጥና መጠናከር ነው በማለት በኢሕአፓ ጥላ ስር የተሰለፈው ወጣት ትውልድ በደሙ አኩሪ የትግል ታሪክን ጽፏል።

ይኸው አገር ወዳድና ተራማጅ ትውልድ፣ የሀገር አንድነትና የግዛታዊ ክልል ባዶውን ሳይሆን ከሕዝብ ጥቅም፣ በእኩልነት ላይ ከተመሰረተ ከሕዝብ አንድነት ጋር ከተሳሰረ የጽንፈኛነት መሰረቱ ይናዳል፤ የጥላቻ ሰንሰለቱ ይሰበራል ብሎ በመታገሉ ተከታታይና ያላባራ የጽንፈኞች በትር አርፎባታል። ያ ወጣት ትውልድ የአንዱ ባህል፣ የአንዱ ቋንቋ፣ የአንዱ ሃይማኖት፣ ... ከተናቀ፤ ታዲያ አንድነት በምን ሊመሠርት ሲልም ያላሰለሰ ትግል አካሂዷል። በወቅቱ፣ በአገራችን የዴሞክራሲ መብቶች ሙሉ በሙሉ በመታፈናቸውና ለመብቱ የሚታገለውን ሕዝብና ተቃዋሚዎችን ያለርህራሄ የማጥፋቱ ዘመቻ ቋሚ የአምባገነኑ ፖሊሲ በመደረጉ፤ ልዩነቶችን ብቻ በመንቀስና በማጉላት፣ ለጎሳ ፖለቲካ ሥር መስደድ አመቺ ሁኔታን ፈጠረ። አክራሪዎች ሀገራቸውን ጭራሽ ወደ መካድ ዘቀጡ። ሌሎች ደግሞ ኢትዮጵያዊነትን ወደ ሁለተኛ ደረጃ ዝቅ በማድርግ ጎሳዊነትን አስቀደሙ። በወቅቱ ተራማጅ ትውልድ ያሰባሰበው ኢሕአፓ የብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄ ከዴሞክራሲ ጥያቄ ተነጥሎ ከታየ ፤ ችግሩ የማይቀር መሆኑን አስቀድሞ ተነበየ። “የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል” እንደተባለውም ጥያቄው በቅጡ ባለመያዙና በአግባቡ ባለመስተናገዱ/ባለመፈታቱ የተነሳ ፤ የአገር ሉዓላዊነትም ሆነ የሕዝብ አንድነት አደጋ ውስጥ ወደቀ።

ያለፉትን አምባገነን ሥርዓቶች የተካው፣ ራሱን የጭቁኖች ነፃ አውጪና የብሔር ብሔረሰቦች ቤዛ አድርጎ የሚቆጥረው ወያኔም ቢሆን ጸረ-ዴሞክራሲና አፋኝ በመሆኑ ሕዝቡ ለዘመናት የታገለለትን የእኩልነትን ጥያቄ ሊመልስ አልቻለም - ተፈጥሮዓዊ ባህርዩ አይፈቅድለትምና። መገንጠልና አንድነት የማይጣጣሙ በመሆናቸው ሥልጣን ላይ በመቆየት አገሪቱንና ሕዝቡን ለመበዝበዝ እንዲያስችለው ሕዝብን እርስ በርስ በማናቆር፤ በማጋጨትና የመከፋፈል ሥራ ላይ ተሰማርቷል። በሁለቱ ሥርዓቶች መካከል ያለው ልዩነት፤ ደርግ በጉልበት ተቃዋሚውን ሁሉ በጭካኔ እየቀጠቀጠ ሕዝብን በማስፈራራት በወታደራዊ አምባገነንነት ሀገሪቱን ያዳሸቀ ቡድን መሆኑ ግልጽ ሲሆን ወያኔ ደግሞ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከደርግ ባልተለየ መንገድ እየረገጠና እየጨቆነ፤ ጎሳዊ አምባገነንነትን አስፍኖ ሕዝቡን እርስበርሱ እያጋጨ ከመግዛት በላይ አገሪቷን ለግንጠላ እያዘጋጀ የሚገኝ ከፉ ኃይል ነው።

ወያኔ ሕዝቡ ለለውጥና ለዴሞክራሲ የሚያደርገውን ትግል ለማፈንና ለማዳከም እንዲሁም በሕዝብ መካከል ውዥንብር እንዲፈጠር ቀን ከሌሊት ሲማስን ይታያል። የሕዝብን ትግል ማፈንና ማዳከሙ አልሳካለት ሲል የትግሉ አቅጣጫ የሀገሪቱን አንድነት ወደሚጊንድ የእርስ በርስ ፍጅት እንዲዞር ደባ በመፈጸም ላይ ይገኛል። ስለዚህም ይህን ውዥንብር በማጥራትም ሆነ የትግሉን አቅጣጫ ዘላቂ ሰላምና እኩልነት ሊያመጣ ወደሚችል የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ጥያቄ በማዞር ወያኔ የቀደደልንን የእርስበርስ ፍጅት ልናመክንና ልናስወግደው ይገባል። ፅንፈኝነትን መሠረት ያደረገ ማናቸውም ዓይነት እንቅስቃሴ የሕዝብን ብሶት ወስዶ በማጋነን ቢስተጋባም ምን ጊዜም ቢሆን የሕዝብን ጥቅምና ፍላጎት እስካላካተተ ድረስ የሕዝብ ትግል ሊሆን እንደማይችል ያ ሀገር ወዳድና ሕዝብ አክባሪ የሆነው ተራማጅ ትውልድ አስተምሯል። አጋልጧል፤ ታግሎታልም።

ያ በ1960ዎቹ በስፋቱ ገኖ ፤ በጥልቀቱ ዳብሮ አሮጌውን የዘውድ አገዛዝ ሥርዓት ለመለወጥና በምትኩ ሕዝባዊ ሥርዓትን ለመገንባት የተደረገው የተማሪዎች እንቅስቃሴ የተጀመረው በጥቂቶች ቆራጥ ወጣት ምሁራን መሪነትና አደራጅነት ነበር። እኒያ ጥቂት የነበሩ ተራማጅና ለውጥ ፈላጊ ወጣቶች ለሚወዱዋት አገራቸው እድገት፣ ብልፅግናና ሥልጣኔ፤ ለሕዝባቸው ፍትህና እኩልነት የከፈሉት መስዋዕትነት ውጤት እየዋለና እያደር በመላው የአገሪቱ ክፍሎች ያለማቋርጥ በርካታ ታጋዮችን እያፈራ የ66-ኡን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ዕውን አርጎ፤ ለዛሬው ቀጣይ ትግል ተጨባጭ ምሳሌ ሁኖ ተገኘ። ትናንት

መሬት ለአራሹ የሚለውን መፈከር ሲያስተጋቡ የነበሩት ምሁራን አርሶ-አደሩ ከገባርነት ተላቆ የመሬቱና የምርቱ ባለቤት እንዲሆን በመጠየቅ ሲታገሉ የነበሩ ሲሆን በገሀድ ይታይ የነበረውን የብሔረሰብ፣ የሃይማኖትና የፆታ ጭቆና መጋረጃውን ገልጠው ወደ አደባባይ በማውጣት በአስቸኳይ መፍትሔ እንዲፈለግለት አገራዊ ጥሪን አሰምተዋል፤ ታግለዋል። የኢትዮጵያንም አንድነት በጭቆና ላይ መሥርቶ በኃይል ለማረጋገጥ መጣር ልዩነትን የሚያሰፋና አንድነትን የሚያናጋ፤ ኢ-ሰባዊም ነው ሲሉ ኮንነዋል። ኢሕአፓን የመሠረቱት እኒያ ለወጥ አቀንቃኝና ተራማጅ ምሁራን የድርጅታቸው ልሳን በሆነው በዴሞክራሲያ የሕዝቡን ጥያቄ በየጊዜው እያነሱ ቀስቅሰዋል፤ አንቅተዋል፤ የመደራጀትንም አስፈላጊነት በተግባር ተርጉመዋል። በትግሉ ሜዳ በመገኘትም ትግሉ የሚጠይቀውን የህይወት መስዋዕትነት ጭምር በቆራጥነት ከፍለዋል።

የየካቲቱ 1966 የተማሪዉ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ሊሰፋ የቻለው ጠንካራ ድርጀትና ቆራጥ የሆኑ የአመራር አባላት ስለነበሩትም ሲሆን ፤ ሰፊ አባላቱና አገር ወዳድ ደጋፊዎቹም ከራሳቸው ጥቅም ይልቅ የአገራቸውንና የሕዝባቸውን ጥቅምና ፍላጎት ያስቀደሙ ፤ ለመስዋዕትነትም ዝግጁ የነበሩ በመሆናቸውም ጭምር ነበር። በመሆኑም ነው በአጭር ጊዜ ውስጥ አገር አንቀጥቅጥ የተባለ ፤ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ያቀፈና ያሳተፈ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በማካሄድ ጠላት እንዲሸበር ለማድረግ የተቻለው።

የሕዝቡ ብሶትና እሮሮ መንስኤውም በሕዝቡ ላይ የተንሳራፋው ግፍ፣ በደልና ጭቆና መሆኑን በሚገባ የተረዳው ያ ለውጥ ፈላጊ ተራማጅ ዜጋ ጭቆናን ለማስወገድም፤ ሕዝቡ የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች ማስተጋባትና መታግል ይገባል ሲል ፅኑ እምነት አደረበት። ሕዝባዊ ትግልም መካሄድ ያለበት መሆኑን ያመነው ይህ ትውልድ፤ የመታገያ መሣሪያ የሆነ የፖለቲካ ድርጅት እንደሚያስፈልግ በመገንዘብ በትግሉ ሂደት ድርጅቱ ኢሕአፓን በሚያዚያ ወር 1964 እንዲመሠረት አደረገ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል በተቀናጀና በተማከለ መልኩ እንዲሰባሰብ፤ ብሎም ሕዝቡ በገዥዎች ላይ ለሚያደርገው ትግል የማስተባበሪያ፤ የማታገያ መሳሪያ ሆኖ እንዲያገለግል በማሰብ ጭምር ነበር የዛሬ አርባ-ዓምስት (45) ዓመት ኢሕአፓ የተመሠረተውና ራሱንም ለሕዝብ በይፋ ያስተዋወቀው። እነሆኝ “ኢሕአፓ ለሕዝብ አለኝታ!” ያለው፤ በነሐሴ 26/1967 ዓ.ም። ኢሕአፓን የመሠረተው ያ ተራማጅ ትውልድ የነበረው ራዕይ የሕዝቡን ጥያቄ ወደጎን አርጎ በሕዝብ ላይ ለመሰየም ወይንም ሕዝብ አያውቅም እኔ ነኝ ወኪሉ በሚል ቀቢፀ -ተስፋ ተሞልቶ አልነበረም። ራዕዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያነሳቸው የሙብት የእኩልነትና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች በአግባቡ እንዲመለሱ ፤ የሕዝቡም የሥልጣን ባለቤትነት እንዲረጋገጥ ሕዝቡ መደራጀትና መታገል ይኖርበታል ፤ ትግሉም በድርጅት መታገዝ፤ መቀናጀት አለበት ከሚል ጽኑ እምነት የተነሳ ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር የታገለለትና አያሌ መስዋዕትነት የከፈለለት የሕዝብ የሥልጣን ምንጭነት የሚያስቀድመው ራዕይ ዛሬም አልተረጋገጠም !!

ኢሕአፓ በረዥሙና በእርግጥም በመራራው የትግል ሂደቱ ለሕልውናው ማጠየቂያ የሆነውን የሀገርና የሕዝብ ፍቅር ተንከባክቦና ጠብቆ ያቆየ ሲሆን በጀግንነትና በመስዋዕትነት የጻፈውንም ታሪክ በተመከሮና ዕውቀት ለማዳበር ችሏል። የፍትህን፣ የዴሞክራሲንና የእኩልነትን፤ የሀገር ሉዓላዊነትን ብርሃን በሀገሪቱ ለማብራት፤ ሁሉን የኢትዮጵያ ልጆች በማሰባሰብ፤ ባንድ ሀገራዊ የትግል ሰንደቅ ሥር በማሰለፍ፤ የሕዝቡ ዓይነታ መለያው ሆኖ የመጣውን ድፍረትና ቆራጥነት በማላበስ ባካሄደው የ45 ዓመት ትግሉ በሕዝባችን ደማቅና ረዥም የትግል ምዕራፍ ውስጥ የማይረሳና የማይሻር አኩሪ ምዕራፍን ፅፏል።

ኢሕአፓ ስሙ እንደሚጠቁመው ኢትዮጵያዊና የሕዝብ ፓርቲ ነው። በኢሕአፓ ጥላ ስር ተሰባስበው የታገሉት ብሔረሰብ ሳይለዩ ከትምክህትና ከጠባብነት ተቃርነው በሕዝብ እኩልነትና ታላቅነት ምለው፤ ኢትዮጵያ የሁሉም የደስታ ቤት እንድትሆን ያመኑ እንጂ ዛሬ አንዳንድ ታሪክ ቀልባሾች ሊሉ እንደሚከጅሉት ኢትዮጵያን ለመጉዳት የተሰለፉ አልነበሩም ! የኢሕአፓ የትናንቱም ሆነ የዛሬው መለያ ለብዙኃን ሕዝብ ጥቅምና ለመላ ዜጎቿ ዕኩልነት፣ ለሀገር ሉዓላዊነት ማለትም ለኢትዮጵያዊነትና ለኢትዮጵያ መቆሙ በመሆኑ፤ ሕዝቡን ለመጨቆንና ሀገሪቱን ለማዋረድ ፤ ለመበተን የፈለጉ ኃይላት ሁሉ በጠላትነት መድበው ሊያጠፉት ቢማስኑም፡ "ልጓዝ በድል ጎዳና በወደቁት ጓዶች ፋና!" ሲል በጽናት ሕዝባዊ ትግሉን የቀጠለ አንጋፋ የፖለቲካ ድርጅት ለመሆን በቅቷል።

የኢሕአፓን ሕያውነት ሰናነሳ ፤ ኢሕአፓ ሲመሠረት ጀምሮ ይዞት የተነሳው የሕዝብ ጥያቄ በቀጣይነት በሕዝቡ ውስጥ ተቀባይነትን አግኝቶ፣ ሥር ሰዶና ደርጅቶ ፤ ሕዝቡ የራሱ ጥያቄ መሆኑን ተገንዝቦ ዛሬም ያልተቋረጠ የህይወት መሰዋዕትነትን ጭምር እየከፈለለት በመታገል ላይ ይገኛል ማለታችን ነው። ኢሕአፓ ሲመሠረት ጀምሮ በመርሀ-ግብሩ አስፍሮ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መታገያነት ካቀረባቸው ፤ ምልዓተ-ሕዝቡም ያስተጋባው የዴሞክራሲ መብት ጥያቄ ዛሬም አልተመለሰም ማለታችን ነው። ዋነኛ የየካቲት 1966-ኡ መተከላዊ የሆኑት የሕዝብ ጥያቄዎች - መሬት ላራሹ፣ ሕዝባዊ መንግሥት ይመሥረት (የሕዝብ የሥልጣን ምንጭነት ይረጋገጥ)፣ የዜጎች እኩልነት ይከበር፤ የሃይማኖት እኩልነት ይረጋገጥ፣ የፆታ እኩልነት ይከበር ...ወዘተ - የሚሉት እስካልተመለሱ ድረስ ከአምባገነኖች ጋር የሚያደርገውን ሕዝባዊ ትግል ሳያቋርጥ መቀጠሉ አይቀሬ ነው።

ካለፈው የትግል ተመክሮ የምንማረው ቁምነገር፡ ሕዝብ ለመብቱ ሲታገል ገዥዎች በኃይል ሊያፍኑት መጣራቸው የሚጠበቅ መሆኑ፤ ነፃነትና መብት በልመናና ተንበርክኮ በመማፀን የሚገኙ አለመሆናቸው እናም መብትን ለማስከበር መራር ትግልና ከበድ ያለ ዋጋን የሚያስከፍል መሆኑን፤ ...ነው። እውነተኛ ትግል መስዋእተነትንም ያካትታል፤ ውጣ ውረድ እርዛት፣ ረሃብና ጥማት፣ ... ወዘተ የትግሉ አካል ናቸው። ትግል ከተፈራ መስዋዕትነት ከተሸሸ አማራጩ ለገዥዎች አሜን ብሎ መገዛት፤ በባርነት ለመረገጥና ለመሰቃየት ጀርባን አጎንብሶ መስጠት ነው።

መብት ስንል መሠረታዊ ነው። መብት የሰው ልጅ ሰብዕናም ጭምር ሲሆን ሀገሩ ደግሞ የሰውነቱ፤ የዜግነቱና የማንነቱ መገለጫ ናት። ትግል ስንልም ሕዝብ ይበጀኛል፤ ያዋጣኛል በሚለውና በፈቀደው መንገድ ሁሉ የመታግል መብቱ የማይገረሰስና በማንም ሊታገድ የማይችል ሲሆን ወሳኙ ራሱ የተበደለው ሕዝብ ብቻ ነው። ገዥዎች የትግሉን ዓይነትና የመታገያ ሥልቱን ወሳኝ ሊሆኑ ከቶም አይችሉም። የትግሉ ዓይነትና ሥልት የሚወሰነውም በገዥዎች ባህርይ ላይ ተመረኩዞ መሆኑም ግልጽ ነው። አምባገነን ገዥዎች የሕዝቡን መብት አፍነው ረግጠውና ደፍጥጠው እንዳሻቸው እያሳደዱ፤ እያሰሩና እየገደሉ፤ ሕዝቡ ለመብቱ መከበር የሚያደርገውን የሰላማዊ ትግል ጎዳና ዘግተው፤ አትጻፍ፣ አትደራጅ፣ አትጠይቅ አታምፅ - ብረት አታንሳ - ማለት አይችሉም። የመብቱ ባለቤት በገዛ አገሩ ባዳና የበይ ተመልካች ሆኖ የተገለለው ፣ የተገፋውና የተረገጠው ሕዝብ ተጨባጩን ሁኔታ በማጤን፣ ሁኔታው የግድ በሚለውና በሚፈቅደው መንገድ ሁሉ መታገል መብቱ ነው።

የየካቲት 1966-ኡ ሕዝባዊ ትግል በዋና መልኩ የትጥቅ ትግል እንዳልነበረ ይታወቃል። በሰላማዊ ትግል ስልት ሰላማዊ ሰልፍ፤ የሥራ ማቆም አድማ፤ ሥራን የማቀዝቀዝ፤ ... ወዘተ የሚታወሱ ናቸው። ሰላማዊ ትግል ሊካሄድ በቻለበት ሁሉ ይህንን የትግል ስልት መጠቀም ወጤታማ መሆኑ አያጠያይቅም፤ በተግባርም እራሳችን ያየነው ነው።

በአገራችን የታየው የፀረ-ወያኔ ሕዝባዊ እምቢተኝነት፣ የሙት ከተሞች አድማ (በሰላማዊ ትግል ስልት) ማድረግ ወያኔን አሸብሯል። ኢኮኖሚውንም በተወሰነ ደረጃም ቢሆን አናግቷል። ባእዳኑንም አስደንግጧል። ሕዝብ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተከታታይ ባደረገው አመጽ (ሠላማዊ ሠልፍ) ለተኩስ አደጋ የተጋለጠ ቢሆንም በስልት ተቀናጅቶና በህቡዕ ተደራጅቶ ባካሄደበት ወጤታማም ሁኗል። እንደሚታወቀውም የዚህ ዓይነቱ ስልት ለሥራ ማቆም አድማም ጥርጊያ ይሆናል። ሰላማዊ ሰልፍ ባላመቸበት ሁኔታ ይህን የትግል ዘርፍ ሊተካ የሚችል ወይም በተጠናከረ መንገድ ረዳት ሊሆን የሚችለው ደግሞ የሥራ ማቆም አድማ ነው። የሥራ ማቆም አድማ ጠቅላላና ሁሉን አቀፍ ከሆነ ውጤቱ ምንኛ ከፍተኛ እንደሆነ ከስድሳ-ስድስቱ (1966-ሑ) ሕዝባዊ አምጽ ተመክሮን መቅሰም ይቻላል። የሥራ ማቆም አድማ ስንል የተወሰኑ የኅብረተሰብ ክፍልን በማጠቃለል ሊጀመር ይችላል። በበቂ ዝግጅት ሁሉም የኅበረተስብ ክፍል - የቢሮ ሠራተኛው፣ የፋብሪካውና የትራንስፖርት ሠራተኛ፣ ነጋዴው፣ ተማሪውና አስተማሪው፣ ጭቁን ወታደሩ፣ …ወዘተ - የሚሳተፍበት በተወሰነ ጊዜ አድማ መጀመር ይችላሉ። ይህ የከተማ ሕዝብ አይነተኛ የትግል መሣሪያ ነው። ቀደም ሲል በተግባር ታይቶ ወጤትን አሳይቷል ዛሬም ይቻላል።

አሁን ያለንበትን ተጨባጭ ሁኔታ በጥሞና ስንመለከተው ዘረኛውና ፀረ- ኢትዮጵያ የሆነው ወያኔ ሕዝቡን በልዩ ልዩ መንገድ እያሰቃየ መሆኑን እንገነዘባለን። በግብር በኪራይና በተለያዩ ክፍያዎች ነጋዴዎችን ይበዘብዛል፤ የንግዱን የኢንዱስትሪውንና የአገልግሎት ሰጭውን ዘርፍ በራሱ ቁጥጥር ስር አስገብቶ የቡድኑን አባላት ባለፀጋ እያደረገ ሌላውን ሕዝብ በድህነት በችግርና በረሀብ እንዲሰቃይ ያደርጋል። እናም በነጋዴው ላይ የተለያዩ ተፅዕኖዎችን ያካሂዳል። በሀገራችን ዛሬ ከኑሮው የተፈናቀለው፤ ሥራ እንዲያጣ የተደረገውና በችግርና በመከራ የሚኖረው ሕዝብ ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም። የዜጎች ማኅበራዊ ኑሮም ገዥዎች/አምባገነኖች ሥልጣን ላይ ለመቆየት በሚያደርጓቸው ፖለቲካዊ ወታደራዊና ኤኮኖማዊ ሁኔታዎች አስከፊነትና ጎጅነት የተነሳ ፍልስልሱ ወጥቷል። አብዛኛው ሕዝብ በታላላፊ በሽታዎች አየተለከፈ የሚረግፍ ሲሆን ረሀብ/ቸነፈርም የአገራችንን ምድር የሙጥኝ ብሎ ገዥዎች በተፈራረቁ ቁጥር አሃዙን እየቀያየረ መንብኘቱን አላቋረጠም። ለራሱ የሚበላው፣ ለከብቱም ግጦሽ አጥቶ ቀየውን እየለቀቀ የሚፈልሰው ሕዝብ ብዛት ከጊዜ ወደጊዜ ከፍ እንዲል ከማድርጉም በላይ ወላጆች ከልጆቻቸው፤ ሚስት ከባልዋ እየተነጠሉ ጧሪና ቀባሪ፣ ተንከባካቢ ረዳት፣ መጋቢና አሳዳጊ እያጡ ነው። ሥራ አጥነቱ እጅግ በመብዛቱ የተማረውና ከተመኛው ራሱን ችሎ በመቆም፤ ትርጉም ያለው ኑሮ/ህይወት መመሥረት ኑሮውንም ማሻሻል ባለመቻሉ ተስፋው የመነመነበት ሆኗል። በመሆኑም ለአገሪቱ የወደፊት ተስፋ መሆናቸው አጠያያቂ ያልሆነውንና በቀላሉም ሊተኩ የማይችሉ ወጣት ልጆቹዋን፤ የተማሩና የሰለጠኑትንም ጭምር እንዲህ እያመነመነች ልትለማና ልትበለጽግ ብሎም ልታድግ ቀርቶ እንዴትስ ራሷን ችላ መቆም ትችላለች?

በዚህ ሁኔታ የወጣቱ ትውልድ ተልዕኮ በታሪክም እንደተመዘገበው በአገራችንም በተጨባጭ እንደታየው ሰጥ ለጥ ብሎ መገዛትና አምባገነኖችን ማግልገል አይደለም። የኢትዮጵያ ወጣቶች የሚታወቁትና ታላቅ ዝናን ያተረፉት ለፍትህ፣ ለእኩልነትና ለዴሞክራሲ መቆማቸው ጭምር ነው።ዛሬም ሕዝቡን በኢኮኖሚ ጥያቄዎች ዙሪያ አሰባስቦ ማታገል መሰረታዊና ተቀዳሚ የትግል ስልት ነው። የህልውናም ጉዳይ ነው። ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል የሚነካና ቀጠሮም የማይሰጥበት ጉዳይ ነው ሊባል ይችላል። በዚህ መስክ የሚካሄድ ትግልም ከፖለቲካ ልዩነት ርቆ ሰፋ ያለውን ትግል ሊያስተባብር የሚችል ነው። በማኅበረሰባዊ ጥያቄዎችም ሆነ በባህል ጥያቄዎች ዙሪያ ተመሳሳይ ትግል ማካሄድ ይቻላል።

ይገባልም። በፖለቲካው ትግልም የማይናቅ ተመክሮ በመስዋእትነት የገበየ ሕዝብ ነው። ቀደም ካለው ታሪክ ሌላ፣ ከላይ ለማሳየት እንደሞከርነው፣ የተማሪዎችን ትግል ስንዘክር፤ የየካቲት አብዮትን ታሪካዊነት ስንመሰክር የምናወሳው ይህንኑ ነው። የተቃውሞን ጎራ ማስፋት ማጠናከር፤ የኅብረት ትግልን መፍጠር፤ የተቃውሞን ግብንም ማወቅና የእንቅስቃሴውንም አቅም መመዘን፤ አንገብጋቢ መፈክሮችን ማስተጋባት የተቃውሞ ሕዝባዊ ሰልፍን ማድረግ፣ መደጋገም፤ የሥራ ማቆም አድማን ማደራጀት፤ አድመኞችን መደገፍና መርዳት፤ ከፋፋዮችንና ወሬ አቀባዮችን (ሰላዮችን) ማግለል፤ የእስረኛንና የሰማዕትን ቤተሰብ መንከባከብ ተገባራዊ የተድረጉበት ወቅቶች ነበሩ። ዛሬም በሀገራችን እነዚህን ለማስቀጠል ከሕዝባችን አቅም በላይ አይደለም።

ይህንን ዘረኛና አምባገነን የሆነ የወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ የሕዝባዊ ትግል አስፈላጊና ግልፅ ከሆነ ቢያንስ ድፍን 26 ዓምት አልፏል። ያለ ሕዝባዊ ትግል የሚገኝ ድልም ሆነ የሙብት መከበር ሊኖር የሚችል ባይሆንም የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቱን ለማስከበርና ለማረጋገጥ ሀገሩን ከጥፋት ለማዳን የጀመረውን ሕዝባዊ አመፅ/ትግል መቀጠልና ማፋፋም ይኖርበታል። ትግል ሲሉ ትግል ስንል የሚል ጨዋታ እንዳይሆን ጥንቃቄ ያሻዋል። ጥቂቶች ብቻ ገንዘቡ አለን፤ መሣሪያው አለን ብለው፣ ትግል አካሂደው ነፃነትና መብትን ለሕዝብ አያጎናፅፉም - ትግል ስንል ሕዝብን ያቀፈ! ሕዝብን መሠረት ያደረገ ! በሕዝብ ተሳትፎ የተደገፈ! ሕዝባዊ ትግል ማለታችን እንደሆነ ግልፅ ሊሆን ይገባል።

ሀገር የሕዝብ እንደመሆኗ፣ ለሀገር ደህንነት የሕዝብ ተሳትፎ ያስፈልጋል። በትግሉ የሕዝብ ግንባር ቀደም ተሳትፎም ካልተረጋገጠ የሚፈለገው ሕዝባዊ ድል አይገኝም። በርግጥ በሚፈለገውም ግብ ላይ አንድ ወጥ ወይንም ተመሳሳይ አቋም አለ ብሎም መጠበቅ አይቻልም። ዴሞክራሲ ያለ ሁሉ የዚሁ መርህ ተከታይ አይደለም። በአንድነት ሽፋን ፍፁማዊነትን፣ የበላይነትን፣ ብዝበዛን ሊያስፋፉ የእኩልነትን መብት ከብዙሃን ሊያርቁ የሚመኙ አልጠፉም። በመብት ስም ሕዝብን ከፋፍለውና እርስ በርስ አፋጅተው የራሳቸውን የበላይነት ለማስፈን የሚጥሩም አሉ። በሕዝብና በዴሞክራሲ ሽፋንም የባዕዳንን ጥቅም ለማስጠበቅ የተሾሙና የተሸለሙም አሉ፤ መወራጨታቸውን አላቆሙም። ስለዚህ የምንፈልገው ዴሞክራሲ የመንመኘው ድል ምን ዓይነት ነው? የማን ነው? ለማን ነው? የሚለውን በግልፅ ማወቅ፤ ማስቀመጥ ያሻል። የምናድናትስ ሀገር በዴሞክራሲና በእኩልነት ላይ ትገነባለች ወይስ በጭቆናና በዘረኝነት? ለዚህ መልስ መሥጠቱና ጎራ መለየቱ ተቀዳሚና ዓቢይ ተግባር ነው።

ከየካቲቱ ሕዝባዊ ትግል የምንቀስማቸው በርካታ የትግል ተመክሮዎች አሉን ከላይ የቀረቡትን የሕዝብ ትግልና የሆነውን፤ ያየነውን ሁሉ ማገናዘብን የግድ ይላል። የሕዝብ ኃያልነት ከኅብረቱ የሚሰርፅ እንጂ ቁጥሩ በዝቶ ተነጣጥሎ በመቆሙ አይደለም። የብዙ ዓመታት የተማሪዎች ትግል የዘውዱን አገዛዝ ሊያናጋ የቻለው ሕዝቡ አሻፈረኝ ብሎ በአንድነቱ በኢትዮጵያዊነቱ በየካቲት በኅብረት በተነሳ ጊዜ ነው። ይህ ኅብረትና ፅኑ የትግል መንፈስ ከየካቲት በኋላ በአስፈላጊው ሥፋትና ጥንካሬ ባለመቀጠሉ ደርግ ተቃዋሚዎቹን ሊጨፈጭፍና በመላው ሕዝብ ላይ ፈላጭ ቆራጭ ሥርዓቱን ለማስፈን ቻለ። ሀገር አቀፍ ተቃውሞ በወቅቱ ተቀናብሮ ባለመከሰቱ የነቁ የሕዝብ ወገኖች አታጋዮች አደራጆችና ቆራጥ ታጋዮች ተጋፍጠው በእሳት ተጠበሱ ትግሉም ከፍተኛ ጉዳት ደርሰበት።

የዛሬዎቹም ታጋዮች፣ በተለይም ወጣቱ ትውልድ፣ ካለፉት ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ትምህርት መቅሰምና የነበሩ ስህተቶችን ላለመድገም፤ ከሕዝባዊ ትግሉ ጠንካራ ጎኖችን መቅሰም ይኖርበታል ብለን እናምናለን። በኢሕአፓ በኩል

ይህንን ዕውን እንዲሆን፣ በተግባር ከትግሉ ከቀሰምነው ተመክሮ በተገኘው መንገድ ሁሉ ለማካፍል ጥረቱ አልተቋረጠም - የሚያዳምጥ ጆሮ ፤ የሚያገናዝብ አእምሮ ከተገኘ !

የወያኔ ሂደትም በተግባር እንደታየው ከደርጎቹ የተለየ አይደለም። የወያኔ ዋና ተልዕኮ ሀገርን ማዳከም፤ ሕዝብን መከፋፍልና መበታተን በመሆኑ፤ የከፋፍለህ አጥፋ ፖሊሲው መረን የለቀቀ ነው። ነጥሎ መምታት፤ እያደናገረ/እያምታታ መከፋፈል፤ ነጥሎ ማጥቃትንም የተካነበት ወያኔያዊ ዘዴው ነው። ኢሕአፓን ለመነጠል ሌሎችን የወደደ መስሎ አቅፌያለሁ ብሏል፤ ይላል። እስካሁን ባየነው፤ ሕዝብን እርስበርስ በብሔር፣ በጎሳ፣ በቀበሌ፣ በሃይማኖት አናክሷል። ድርጅቶችን ቀፍቅፎ፤ ድርጀቶችን እርስበርስ አጋጭቷል። አዳክሟል። ወያኔ ከፍጥረቱ ዋና ችግሩ ፤ ማለትም እምነቱና ቅኝቱ ይሄው ነው። በዚህ ላይ ግልጽ መሆንን ይጠይቃል። ለነገሩ አይከፍሉት መሥዋዕትነት በመክፈል እጅግ በርካታ ለሆነው በፖለቲካው መስክ ለተሰለፈው ክፍል ግልጽ እየሆነ መጥቷል ብንል ስህተት አይሆንም - ከጥቂቱ፣ ዛሬም የዝሆን ጆሮ ከገጠሙት በቀር።

ወያኔ ዘረኛና አምባገነን ኃይል አምላኪ በመሆኑ ሽብርና ጭፍጨፋን የተላበሰ ነው። እንደ ደርግ ሁሉ ወያኔም በሥልጣን ላይ የተቀመጠው በጉልበት/በኃይል ነው። ድፈን 26 ዓመት በቦታው የቆየውም የሕዝብን ፍላጎት ረግጦና ጨፍልቆ ነው። ያም ሆኖ ወያኔ በሕዝብ አመፅ ተናጋቷል። የሚቀረው መውደቅ ነው። ጊዜ ካገኘና ወያኔ መልሶ ከተጠናከረ የሕዝብን ተቃውሞና አመፅ ለመግታት የደርግን የቀይ ሽብር የሚያስንቅ “ትርኢት” ሊያሳየን የሚቦዝን አይደለም። ለዚህ ማርከሻው የሕዝብ መደራጀትና ከዳር እስከዳር እጅ ለእጅ ተያይዞ በአንድነት ሆ! ብሎ መነሳት ነው። በአንድነት የተሰባሰበን፤ በዕድሜውም የቆየን የሕዝብ ትግል የሚገታው ምድራዊ ኃይል ፈጽሞ አይኖርም - ለምሳሌ፣ የቬትናምን የሕዝብ ትግል ያስታውሷል። አምባገነኖችም የሚፈሩት ይህንን የሕዝብ በትርና ቁጣ፤ በጽናት መታገሉን ብቻ ነው።

ዛሬም እንደትናንቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔን አንፈልግህም፤ አልወከልኩህም “ወጊድልኝ!” እያለ በተበታተነ መልኩም ቢሆን እየታገለ የህይወት መስዋዕትነትን እየከፈለ ነው። ዛሬ ከትናቱ የተለወጠ ነገር የለም። ወያኔን ቢያገላብጡት፤ ሌላ አታሞ ቢደልቁለት፤ አዳዲስ ምስክሮች ቢዥጎደጎዱለት፤ ሲገልጡት ያው ወያኔ ነው።፡ ለውጥ የሚጠበቀው ከሕዝብ ነው። የኢትዮጵያ ምድር ለውጥን አርግዛለች፤ ነፃነትና ፍትሕን እያማጠች ያለች አገር ነች። በወያኔ ማን አለብኝነት ሳይቋረጥ የሚካሄደው ግፍ ሞልቶ እየፈሰሰ ነው። ገላጋይ፣ አዋላጅ የቁርጥ ቀን ታጋይ ልጆቿን ትሻለች። የዚያች ሀገር ለወጥ ፈላጊና ሀገር ወዳድ ዜጋ ሁሉ መታገል ማንም የማይገረስሰው መብቴ ነው ብሎ መነሳት ይጠበቅበታል። ህይወቴን ለሀገሬ ለወገኔ ብሎ በቆራጥነት መሰለፍ ይገባዋል። ትናንትና የታየውን፤ ዛሬም ማየት የማይቻልበትና የማይደገመበት ምንም ምክንያት አይኖርም - ኢትዮጵያ የታጋዮች መካን ሆና አታውቅምና !

በሕዝብ ያልተወከለን መንግሥት አምርሮ መታገል፤ ወያኔ ላይ ማመፅ፤ ለሀገር ህልውናና ለሙብት፤ ላልተገደበ ዜግነት፤ ለዕኩልነት መከበር ወዘተ... አምርሮ መዋደቅ ኢትዮጵያዊ ግዴታ ብቻ ሳይሆን የሰብዓዊ ክብር መገለጫም ነው ብሎ ኢሕአፓ ያምናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለማሰለስ በገዥዎቹ ላይ የዘመናት ትግል ያካሄደው፤ የተዋደቀውና አያሌ የህይወት መሰዋዕትነትን የከፈለው፤ በከፋ የድህነት አረንቋ ውስጥ ተዘፍቆ በረሀብ እየተገረፈ፤ በድንቁርናና በበሽታ እየማቀቀና እየተሰቃየ ፍዳውን እየቆጠረ ለመሆን ሳይሆን ፤ የሙብቱ ባለቤት ሆኖ ነፃ በሆነ መንገድ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትን አዲስ የሆነ ሕዝባዊ ሥርዓት ለመገንባት ነው። የኔ የሚለው ሕገ መንግሥት አርቅቆና እውን አድርጎ የኔ የሚለውን

መንግሥት በሥልጣን ላይ ለመሰየም ነው። ሲያሰኘው ሊጠይቀው የሚችል እንዲሁም ከሥልጣን አውርዶ በቦታው ሌላ ሊሰይም የሚችልበትን የሥልጣን ምንጭነቱን ያስረገጠ ሥርዓት እውን ለማድረግ ነው !

የወያኔ የጥፋት ተልዕኮ ሊደርስ የሚችለው በወያኔ በራሱ ብቻ ሳይሆን ሕዝቡን በሚከፋፍሉና በእጅ አዙር በሚረዱትም ክፍሎች አስተዋጽዖና ተሳትፎ መሆኑ ግልጽ መሆን ይኖርበታል። ዐይናችንን፣ አዕምሯችንን ከፍተን በመከታተል ነቅተን መጠበቅ ይገባል ስንል፤ ያለፈው እንዳይደገም፤ ዛሬ የጠላነው ነገ በሌላ ገጽታ እውን እንዳይሆን፤ ተከፋፍለንና ተወናብደን ለወያኔ ሸርና ጥቃት እንዳንጋለጥ መጣር ይኖርብናል ከሚል ነው። ወያኔን በቅጡ ዛሬም ላልተረዱ የዋሆችና ማንን እንደሚታገሉ፥ ለምን እንደሚታገሉና እንዴት እንደሚታገሉ ላልተገለጠላቸው "ፖለቲከኞች" የወያኔ አምባገነናዊነት፣ ከፋፋይነት፣ ኃይል አምላኪነት፣ ... ወዘተ ልክፍት ሳይሆን "ተፈጥሮው" /ማንነቱ መሆኑን ማወቅ ያሻል እንላለን። የወያኔ መሪዎች ፀረ- ሕዝብ ሽብር እየሰፉ እንጂ የሚቀንስ አይደለም የምንለው አፈጣጠራቸውን ብሎም ድርጊታቸውን በሚገባ ሰለምናውቅና ስለምንረዳ ጭምር ነው። የሕዝብ ተቃውሞ እያየለና እየሰፋ እስከሄደ ድረስ ወያኔ ሕዝብ ማሸበሩን አያቆምም። ያ ደግሞ - እርስ በርሱ የሚቃረን ነገር ቢመስልም፤ ለወያኔ ውድቀት ጉድጓድ ማሽ የፍፃሜውም ጎዳና መሆኑ ግልፅ ነው። ለዚህም ነው ነቅቶና በህቡዕ ተደራጅቶ የወያኔን ሴራ ማጋለጥ፤ ማክሸፍ፤ ለወያኔ መሣሪያ ላለመሆን መጠንቀቅ፤ የፀረ-ወያኔ ትግሉን ጥንካሬና ኅብረት ለማረጋገጥ መጣር ቀዳሚ ትኩረት መሰጥት የሚገባው። ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ግዴታውን ሲወጣ ነው ሀገር ከመበታተንና ከጥፋት የምትድነው።

የኢሕአፓ የትግል ይዘት፣ ራዕይ በኢትዮጵያ ሀገራዊ ጥቅም፣ ሉዓላዊነትና የሕግ የበላይነት መረጋገጥ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ይህ ነው የማይባል መስዋዕትነትን ከፍሏል። መከራና ስቃይ ተቀብሏል፤ አምባገነን በአምባገነን ሲተካ ፤ ቅጥረኛ በቅጥረኛ ሲተካካ ፤ ሳያወላውል ትግሉን ቀጥሏል። የትግላችን ይዘትም እንዲሁ ታድሶ፤ ዳብሮና ተጠናክሮ ይገኛል እንጂ ተለውጦ፤ ተሰርዞና ተደልዞ አይገኝም። ኢሕአፓ ለሕዝብ እኩልነትና አንድነት ፤ ለዴሞክራሲና ለሕዝብ የሥልጣን ምንጭነት ታግሏል። ዛሬም ለዚሁ ትግሉን እንደቀጠለ ይገኛል። እነዚህ ክቡር ዓላማዎች ከግብ እስካልደረሱ ድረስ ትግሉ መቼም ቢሆን መች የሚቆም አይሆንም። ለጠላቶቻችን ቅዥት ለወገን ደግሞ አለኝታና ደም መላሽ ሆኖ ኢሕአፓ ትግሉን ይቀጥላል - እጅ ለእጅ ተያይዘን የዚህን አምባገነን ሀገር አጥፊ አገዛዝ ማክተሚያ እናፋጥን እንላለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሙብቱ የሚያደርገው ህዝባዊ ትግል ይቀጥላል!
ድልንም ይቀዳጃል!

እናቸንፋለን!!